# የጣሊያን የኢንዱስትሪዎች ኮንፌዴሬሽን (ኮፊ ኢንዱስትሪያ) እና የኢትዮጵያ የዘርፍ ማህበራት የመግባቢያ ሰነድ ተፈራረሙ

የኢትዮጵያ የዘርፍ ማህበራት ማህበርና የጣሊያን የኢንዱስትሪዎች ኮንፌዴሬሽን ተቀራርቦ በጋራ ለመስራት የሚያስችላቸውን የመግባቢያ ሰነድ እ.ኤ.አ ዲሴምበር 3 ቀን 2013 በሮም የኮንፌዴሬሽኑ ጽ/ቤት ተፈራርመዋል፡፡



በኢትዮጵያ የዘርፍ ማህበራት በኩል የመግባቢያ ሰነዱን የፈረሙት የማህበሩ ፕሬዝዳንት አቶ ገብረህይወት ገብረእግዚአብሔር ሲሆኑ በጣሊያን የኢንዱስትሪዎች ኮንፌዴሬሽን በኩል ደግሞ በኮንፌዴሬሽኑ የአስአፍሪካ ፕሬዝዳንት Mr.Fausto Aquino ናቸው፡፡

በዚሁ ወቅት የአስአፍሪካ ፕሬዝዳንት ባሰሙት ንግግር በኢትዮጵያ እየተመዘገበ ካለው ዕድገት አኳያ የጣሊያን ካምፓኒዎች ወደ ኢትዮጵያ ሄደው

ለመስራት ፍላጎታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱን፣ ከዚህ አኳያ ማርች 8 ቀን 2012 በሮም የተካሄደው የኢትዮ- ጣሊያን ቢዝነስ ፎረም፣ በዚህው ወቅት በጣሊያንና በኢትዮጵያ ካምፓኒዎች መካከል የተካሄዱት ከ250 በላይ የBusiness to Business ውይይቶችና እንዲሁም የሁለቱ አገራት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች መካከል የተደረጉ ውይይቶችና የተደረሱ መግባባቶች፣ በመቀጠልም በወቅቱ የጣሊያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የተመራ የጣሊያን የቢዝነስ ልዑካን ቡድን በሜይ 2012 በኢትዮጵያ ጉብኝት ማድረጉ አዎንታዊ ፋይዳ እንደነበራቸው በማውሳት፣ ኮንፌዴሬሽኑ ከኢትዮጵያ የዘርፍ ማህበራት ጋር በመተባበርና በቅርበት በመስራት የጣሊያን ባለሀብቶች በኢትዮጵያ በኢንቨስትመንትና በንግድ እንዲሰማሩ ለሁለቱ አገራት ጥቅም ለመስራት ዝግጁ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

የኢትዮጵያ የዘርፍ ማህበራት ፕሬዝዳንት አቶ ገ/ህይወት በበኩላቸው የዘርፍ ማህበሩ ስለሚያከናውናቸው ተግባራትና ለውጭ ባለሀብቶች ስለሚሰጣቸው ድጋፎች፣ የጣሊያን ካምፓኒዎች በኢትዮጵያ ሊሰማሩባቸው ስለሚችሉ መስኮች በማብራራት በዚህ ረገድ ከጣሊያን የኢንዱስትሪዎች ኮንፌዴሬሽን ጋር ተቀራርቦ ለመስራት ማህበሩ ዝግጁ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በጣሊያን የኢፌዲሪ አምባሳደር ክቡር አምባሳደር ሙሉጌታ አለምሰገድ በበኩላቸው በጣሊያንና በኢትዮጵያ መካከል ስላለው የረጅም ጊዜ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ በተለያዩ መስኮች እየተጠናከረ መምጣቱን፣ ሆኖም በኢኮኖሚ መስክ ያለው ግንኙነት በሚፈለገው ደረጃ አለመድረሱንና ይበልጥ ሊጠናከር እንደሚገባው፣ ይህ እውን እንዲሆን የሁለቱ አገራት ተቋማት ተቀራርበው በጋራ መስራት እንደሚኖርባቸው አፅኖት በመስጠት ከዚህ አንፃር በዕለቱ የተፈረመው የመግባቢያ ሰነድ ዋንኛ መሰረትና በሁለቱ አገራት ካምፓኒዎች መተማመንን እንደሚያጎለብት፣ ይህንኑ መሠረት በማድረግ በቀጣይ ትርጉም ያለው ስራ ለመስራት በር እንደሚከፍት ገልፀዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በአገራችን ስላሉ የኢንቨስትመንት እድሎችና የቅድሚያ ትኩረት መስኮች፣ስላሉ ማበረታቻዎች፣ በአገራችንና በጣሊያን መካከል ስላሉ የረጅም ጊዜ ትስስሮች፣ ጣሊያኖች ስለ ኢትዮጵያ ያላቸውን ግንዛቤ ከማስፋት

አኳያ በጣሊያን የኢፌዲሪ ኤምባሲ በኩል በተለያዩ የጣሊያን ክልሎች ስለተካሄዱ ፕሮሞሽኖችና በያዝነው ዓመትም ለማካሄድ ስለታቀዱ ተመሳሳይ የፕሮሞሽን ፎረሞች በማብራራት የጣሊያን ካምፓኒዎች ወደ  ኢትዮጵያ መጥተው እንዲሰሩ ጋብዘዋል፡፡



ከዚህ ባሻገር በሁለቱ አገራት መካከል በቢዝነስ መስክ ያለው ትስስር ይበልጥ እንዲጠናከር የሁለቱ አገራት ተቋማት ጠንክረው መስራት እንደሚኖርባቸው በመሳሰብ ኤምባሲያችን በዚህ ረገድ ተባብሮ ለመስራት ዝግጁ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በመቀጠልም በሥነ-ሥርዓቱ ላይ የተገኙ ስምንት የጣሊያን ካምፓኒዎች ኃላፊዎች ስለካምፓኒዎቻቸውና በኢትዮጵያ ለመሰማራት ስለሚፈልጉባቸው መስኮች  በማብራራት ወደ ስራ መግባት እንዲችሉ በኢትዮጵያ የዘርፍ ማህበራት በኩል ሊደረጉላቸው ስለሚችሉ ድጋፎች የጠየቁ ሲሆን ደንቦችና መመሪያዎች

በሚፈቅዱት መሠረት የተቻለው ድጋፍ እንደሚደረግላቸው ምላሽ ተሰጥቷቸዋል፡፡

